Haile Selassie I - Harar Military Academy North America

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሐረር ጦር አካዳሚ ሰሜን አሜሪካ

# የጃኑዋሪ 18 ቀን 2026 ዓ.ም መደበኛ ስብሰብ ማጠቃላያ

## (Summary of January 18, 2026 Bi-monthly Meeting)

“የቀዳማዊ ሐይለስላሴ/ሐረር ጦር አካዳሚ ምሩቃን ማህበር በሰሜን አሜሪካ” በሁለት ወር አንድ ጊዜ የሚያካሂደውን መደበኛ ስብሰባ ጃኑዋሪ 18 ቀን “4467 Old Branch Avenue-Temple Hills, MD 20748 በሚገኘው ስብስባ አድራሻ ውስጥ አካሂዷል። በ2026 መጀመሪያ ወር የተካሄድውን ይህን መደበኛ ስብስባ ያስተናገዱት ሻለቃ ሃይለማሪያም አባይ (1ኛ ኮርስ ምሩቅ) እና ባለቤታቸው ወይዘሮ ትሰሜ ሃይሌ ከልጆቻችው ጋር በመሆን ነበር። በስብሰባው ላይ **35** አባላትና **27** ቤተሰቦችና ተጋባዥ እንግዶች በድምሩ **62** ሰዎች ተገኝተው ነበር። ስብሰባው በርካታ ተሳታፊዎች የተገኙበት፤ ከማህበር ስብስብ ይልቅ ትልቅ ቤተሰባዊ አንድነት የታየበት ስብሰባ ነበር።

ከምሳ በፊት በነበረው ፕሮግራም የ“እንኳን ደህና መጣችሁ!” ሰላምታ ከቀረበ በኋላ እንግዶች ራሳቸውን እንዲያስተዋውቁ በቀረበው ጥሪ መሰረት ሻለቃ ምንተስኖት ዜና (18ኛ ኮርስ አባል) ከአዲስ አበባ፤ ወይዘሮ ያይኔአበባ ደረስ (Yayeneabeba Deres- (የብ/ጀነራል ይላማ ግዛው 1ኛ ኮርስ አባል ባለቤት) ከሚኒሶታና ሌሎችም ከቅርብና ከሩቅ የመጡ አባላት ራሳቸውን አስተዋውቀዋል። አባላትም እንግዶቹን እንኳን ደህና መጣችሁ በማለት  በጭብጨባ አቀባበል አድርገውላቸዋል። ቀጥሎም በቅርቡ ከዚህ ዓለም በሞት ለተለዩት የአካዳሚው 3ኛ ኮርስ ምሩቅና የአሉምናይ ማህበራችን አባል ለነበሩት ሻለቃ ሙሉጌታ ከበደ የአንድ ደቂቃ የሂሊና ጸሎት ተደርጎላቸዋል።

ከ**2፡00-3፡00** ሰዓት የምሳና የግል ጨዋታ ጊዜ ነበር።









ከ***3፡00-5፡00*** ፒ.ኤም በነበረው ጊዜ በሶስት አጀንዳ ርእሶች ላይ ገለጻ ተደርጓል። ከአጀንዳ ገለጻው አስቀድሞ ኖቨምበር 23 ቀን 2025 በተካሄደው መደበኛ ስብሰባ የ"ቀዳማዊ ሃይለስላሴ/ሐረር ጦር አካዳሚ ምሩቃን ማህበር -በሰሜን አሜሪካ" የተመሰረተበት 25ኛ ዓመት በተለየ ሁኔታ ይከበር ወይስ በመደበኛ ስብሰባ ቀን ታስቦ ይዋል?" በሚሉ ሁለት አማራጮች ላይ ውይይት ተደርጎ "ከ2/3ኛ በላይ አባላት በልዩ ሁኔታ ይከበር" በማለት በአብላጫ ድምጽ መወሰናቸውና "በዓል አዘጋጅ ኮሚቴ አባላትን መምረጣቸው በንባብ ከተሰማ በኋላ ቃለ-ጉባኤው በሙሉ ድምጽ ጸድቋል።

ገለጻ የተሰጠባቸው ሶስት አጀንዳ ርእሶች የሚከተሉ ናቸው፦

1. ስራ አስፈጻሚ ኪሚቴው አመራሩን ከተረከበ ጊዜ ጀምሮ በአንድ ዓመት **(2025 ዓ.ም)** ያከናወናቸው ስራዎች በሪፖርት መልክ ቀርበዋል።
   - በ2025 ዓ.ም ስድስት መደበኛ ስብሰባዎች መካሄዳቸው *(Organized and conducted six bimonthly meetings).*
   - የአሉምናይ ማህበሩ ሕጋዊ ሴርቲፍኬት መታደሱን **(Renewal of "*Registration Certificate*").**
   - ለስራ የሚያገለግሉ ኮምፒውተርና የወርቀት ማተሚያ ማሽና በስጦታ (*Received Material and Financial Donations*) መገኘቱንና ለፈቃድ እድሳት የተጠየቀው ገንዘብ በነጻ መሸፈኑን፤ እንዲሁም እርዳታውንም የለገሱት የማህበሩ አባላት ልጆች መሆናቸው ተገልጿል።
   - የአሉምናይ ማህበር መተዳደሪያ ደንብ መሻሻሉንና በአባላት ጸድቆ ለእያንዳንዱ አባል እንዲደርስ መደረጉን ( ***Revision and Amendment of HMAHAA Bylaw).***
   - የማህበሩ ገንዘብ አያያዝ "ኮምፒውተራይዝድ" ተደርጎ (**Computerize**) ገንዘብ ለመሰባሰብና ውጪ ለማድረግ አመቺ ሁኔታ መፈጠሩ፤
   - የአካዳሚ ዌብሳይትና መገናኛ ዘዴዎች ተሻሻለው ***(Update Academy Website )*** ጥሩ ግንኙነትና መረጃ ልውውጥ መኖሩ ተገልጿል።

2. የ**2026** የስራ ክንውን እቅድ (***Year 2026*** **Activity plan**)

በሁለተኛ አጀንዳ አሉምናይ ማህበሩ በ2026 ዓ.ም ሊሰራ ያቀዳቸው እቅዶች በዝርዝር ቀርበዋል። እቅዶቹም ጠቅለል ባለ ሁኔታ የሚከተሉት ናቸው፦

- አሉምናይ ማህበሩ በየሁለት ወሩ የሚያካሂዳቸውን መደበኛ ስብሰባዎች አጠናክሮ መቀጠል (Organize and Conduct bimonthly Meetings)

- በሕመምና በተለያዩ የግል ችግሮች ምክንያት ወርሃዊ ስብሰባዎች መሳተፍ ያልቻሉ አባላትን መጎብኘትና መጠየቅ (Visit members who are unable to attend bimonthly meetings).

- ወርሃዊ ስብሰባ አዘጋጆችን ተራ ቅደም ተከተል ማውጣትና በጊዜ ማሳወቅ (Prepare bimonthly meeting schedule and inform hosts at least six months ahead of time).

- የማህበር አባሎቻችንን የእርስ በእርስ በሚገባ የሚተዋወቁበትንና ልምድ የሚለዋወጡበትን ፕሮግራም ማዘጋጀት (organize "know better each other" experience sharing program).

- የማህበራዊ ጉዳይ ኮሚቴን እንደ ገና ማዋቀርና ማህበራዊ ግኑኝነታችንን ማጠናከር ( Select Public Relations Committee and strengthen social contacts).

- የቀዳማይ ሃይለስላሴ/ሐረር ጦር አካዳሚ ምሩቃን ታሪክ 2ኛ እትም መጽሐፍ ዝግጅት ላይ ተሳትፎ የሚያደርግና መረጃዎችን የሚያጠናክር ኮሚቴ መሰየም (Assign committee and Collaborate in the process of Edition and publication of the Hailselassie/Harar Military Academy Graduates  History Book).

- የአካዳሚ ምሩቃን ልጆች እንዲሰባሰቡና የራሳቸውን ማህበር እንዲመሰርቱ ምክርና እገዛ ማድረግ (Assist “Second Generation Children” to form their own association under the umbrella of HMAHAA).

- የአካዳሚ ምሩቃን ማህበር በሰሜን አሜሪካ የተመሰረተበትን **25**ኛ ዓመት ቀን ለማክበር ለተመረጠው በዓል አዘጋጅ ኮሚቴ ምክርና ድጋፍ መስጠት (Celebrate the 25th Anniversary of the formation of HMAHAA).

- ለአሉምናይ ማህበራችን የመሰብሰቢያ አዳራሽና ጽ/ቤት የሚገኝበት መንገድ መፈለግ (Look for possibilities of acquiring office space and meeting place for Haileselassie/Harar Military Academy Alumni Association (HMAHAA).

3. በመጨረሻ የቀረበው የማህበሩ ፋይናንስ ሪፖርት ነበር።

    - ከወርሃው መዋጮና ከሌሎች ገቢዎች በተሰበሰበ ገንዘብ የማህበሩ ገንዘብ አቅም ማደጉ፤ (Income increase from Monthly contribution collections, donations and other sources).

    - የአሉምናይ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ በሚፈቅደው መሰረት ችግር ለደረሰባቸው ቤተሰቦች የሚገባቸው ክፍያ መፈጸሙን፤ እንዲሁም ለአስተዳደራዊና ለሌሎች ጥቃቅን ወጪዎች ክፍያ መፈጸሙን (Payments of benefits and other administrative costs).

    - የማህበሩ ገንዘብ አያያዝ ኦዲት ተደርጎ አባላት እንዲያውቁት ማድረግ እንደሚያስፈልግ ሪፖርት ተደርጓል። (Conduct Audit and know financial status of the Alumni Association)

- አባላት ስልኮቻቸውን ተጠቅመው ወርሃዊ መዋጮ በቀላሉ መክፈል የሚችሉበት የ"ዜል ክፊያ" ሲስተም ለመዘርጋት እንደታቀደ በተጨማሪ ገልጿል። (Introduce "Zelle APP" payment system and inform members to pay their monthly contributions by phone).

- በመጨረሻም የዓመቱ ጠቅላላ ውጪ **$ 15,605.82** እንደ ሆነና ማህበሩ በአሁኑ ሰዓት ባንክ አካውንት ውስጥ ያለው ተቀማጭ ገንዘብ **$ 138,451.70** መሆኑ ሪፖርት ተድርጓል።

 

በቀረበው ሪፖርት ላይ ተወያይቶ ውሳኔ ለመስጠት ጊዜ ስለ አነሰ ወይይቱና የኦዲተር ምርጫው በሚቀጥለው ስብሰባ እንዲደረግ ውሳኔ ተላልፏል። በሪፖርቱ ማጠቃላይ የፋይናንስ አሰራሩን በተመለከተ ጉባኤው ኢዲተር መርጦ የማህበሩን ሂሳብ ኦዲት እንዲያስደርግ ሊቀ መንበሩ ማሳሰቢያ ሰጥተዋል። በተጨማሪም ስራ አስኪያጅ ኮሚቴው ውጤታማ ስራ መስራት የቻለው ሙሉ ጊዜ በመስጠትና በትጋት በመስራቱና የማህበሩ አባላትም ሙሉ ትብብር በማድረጋቸው ስለሆነ ለኮሚቴውና ለማህበሩ አባላት ሊቀ መንበሩ ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

በመጨረሻም የስብሰባውን መስተንግዶ በአስደሳች ሁኔታ ላዘጋጁትና ላስተናገዱት ለሻለቃ ሃይለማሪያም አባይ፤ ለወይዘሮ ትሰሜ ሃይሌና ለልጆቻቸው ምስጋና ቀርቦ የእለቱ ስብሰባ በ**5:00** ፒ.ኤም ተጠናቋል። የሚቀጥለው የአሉምናይ ማህበር ስብሰባ

አስተናጋጅ ሻለቃ አሰፋ አየለ መሆናቸው ለተሳታፊዎች ተገልጿል።

የአሉምናይ ማህበሩን ስብሰባ ተሳታፊዎች በከፊል የሚያሳዩ ፎቶግራፎች













Maison
Perrier
CANADA
DRY




 